## ስለ ማኅበሩ አባልነት

### አንቀጽ 9፡ የማኅበሩ አባላት

9.1. መደበኛ አባላት

የሚከተሉትን መመዘኛዎች የሚያሟላ ሰው የማኅበሩ መደበኛ አባል መሆን ይችላል

1. ከሚመለከተው ሕጋዊ አካል እውቅና ካገኘ የትምህርት ተቋም በፋርማሲ የመጀመሪያ ዲግሪና ከዚያ በላይ የትምህርት ደረጃ ያለው፣
2. አግባብ ካለው አካል የሙያ ምዝገባ ምስክር ወረቀት የተሰጠው፤
3. ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው፣
4. በህግ መብቱ ያልተገፈፈ፤

ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟላና ማኅበሩ የሚወስነውን ዓመታዊ ክፍያ ለመክፈል ፈቃደኛ ከሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ ኗሪ ቢሆንም መደበኛ አባል መሆን ይችላል። ሆኖም ግን የአባልነት ክፍያ ከ90/10 የገቢ ምንጭ በ10% (ከሀገር ውጭ የተገኘ) ተመድቦ ይመዘገባል።

9.2. ተቋማዊ አባላት

1. ማንኛውም በኢትዮጵያ ውስጥ በፋርማሲ ዘርፍ ወይንም በሌላ የጤና ዘርፍና ተያያዥ ሥራ ላይ የተሰማራ ሕጋዊ ሰውነት ያለውና ማኅበሩ ለተቋማዊ አባላት የሚያወጣውን ዓመታዊ ክፍያ ለመክፈል ፈቃደኛ የሆነ ድርጅት የማኅበሩ ተቋማዊ አባል መሆን ይችላል።
2. ተቋማዊ አባላት መደበኛ ተቋማዊ አባላት እና ልዩ ተቋማዊ አባላት ተብለው ይከፈላሉ።

9.3. ተባባሪ አባላት

የሚከተሉትን መመዘኛዎች የሚያሟላ ማንኛውም ሰው የማህበሩ ተባባሪ አባል ሊሆን ይችላል፡

1. ከታወቀ የትምህርት ተቋም በፋርማሲ ሙያ በዲፕሎማና ከዚያ በታች የተመረቀ፣አግባብ ካለው አካል የሙያ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ያገኘ እና ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው፣
2. በሌላ ሙያ የመጀመሪያ ዲግሪ/ዲፕሎማ ኖሮት በፋርማሲ የትምህርት መስኮች የማስተርስ ዲግሪ ወይም ፒ.ኤች.ዲ ዲግሪ ያለው እና ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው፣
3. በሌሎች የጤና ሙያዎች ከታወቀ የትምህርት ተቋም ተመርቆ አግባብ ካለው አካል የሙያ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ያገኘ፣

4. በማህበራዊም ሆነ በተፈጥሮ ሳይንስ ሙያዎች ከታወቀ የትምህርት ተቋም ቢያንስ በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቆ ለፋርማሲ ሙያ እድገት ድጋፍ የሚሰጥ መሆኑ በሥራ አመራር በርዱ ከታመነበት፣
5. አግባብ ካለው አካል ፈቃድ የተሰጠው የባህል መድኃኒትና ሕክምና አዋቂ፣
6. ማኅበሩ ለተባባሪ አባላት ያወጣውን ክፍያ ለመክፈል ፈቃደኛ የሆነ፣

9.4. የተማሪ አባላት

1. በፋርማሲ ዘርፍ በዲግሪ መርሃ ግብር ከታወቀ የትምህርት ተቋም ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ፣ቢያንስከ 3ኛ ዓመት የዩኒቨርሲቲ/ኮሌጅ ትምህርት የደረሱና በዜግነት ኢትዮጵያዊ የሆኑ ተማሪዎች፣
2. ተማሪ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሚማሩበት ተቋም ኃላፊ ማቅረብ የሚችሉ፤
3. ማንኛውም የተማሪ አባል ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ ከሚመለከተው ሕጋዊ አካል የሙያ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ያገኘ የመደበኛ አባላት የሚከፍሉትን ክፍያ በመክፈል ከተማሪ አባልነት ተሰርዞ በመደበኛ አባልነት ይመዘገባል፣
4. በፋርማሲ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸውና የሁለተኛ ዲግሪ (ማስተርስ) ወይንም ከዚያ በላይ የሆነ ትምህርት በመከታተል ላይ ያሉ ተማሪዎች በተማሪ አባልነት መመዝገብ አይችሉም፣
5. የተማሪ አባላት በተለያዩ ምክንያቶች ትምህርታቸውን አቋርጠው ከትምህርት ቤት ከተሰናበቱ የተማሪ አባልነታችው ይሠረዛል፣

9.5. የክብር አባላት

ለማኅበሩና ለፋርማሲ ሙያ እድገትና ሕብረተሰቡ ከሙያው ተጠቃሚ እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማበርከቱ የተረጋገጠለት በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የሚኖር ግለሰብ በሥራ ማዕከላዊ ሥራ አስፈጻሚ አቅራቢነት በጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ የክብር አባል መሆን ይችላል። የክብር አባልነት አሰጣጥ በተመለከተ ማኅበሩ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

9.6. ልዩ አባላት

በስነ-ምግባሩ አርአያ የሆነና በማዕከላዊ ሥራ አስፈጻሚ የሚወሰነውን የልዩ አባልነት ክፍያ በአንድ ጊዜ የከፈለ ግለሰብ ወይንም ድርጅት ልዩ አባል ሆኖ ይመዘገባል። የስነ-ምግባር ጉድለት ያሳየ ልዩ አባል አባልነቱን ያጣል።

### 9.7. የእድሜ ልክ አባላት

የመደበኛ አባልነት መሥፈርትን የሚያሟላና በማዕከላዊ ሥራ አስፈጻሚ በሚወሰነው መሠረት የ10 ዓመት የአባልነት ክፍያን በአንድ ጊዜ የከፈለ ግለሰብ የእድሜ ልክ አባል ይሆናል፡፡ የእድሜ ልክ አባላት በማዕከላዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የተወሰነውን የረዥም ጊዜ ክፍያ ከከፈሉ በኂላ ከዓመታዊ የአባልነት ክፍያ ነጻ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 10፡ የአባላት መብት

### 10.1. የመደበኛ አባላት መብት

1. ማኅበሩ በሚያካሂዳቸው ጠቅላላ ጉባዔዎች፣ሳይንሳዊ ኮንፈረንሶችና ሴሚናሮች መሳተፍ ይችላሉ፡፡
2. በማኅበሩ በማዕከላዊ ሥራ አስፈጻሚ እና ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ውስጥ የሚያገለግሉ አባላትን የመምረጥ እና/ወይም የመመረጥ እንዲሁም በማኅበሩ አሠራር ውስጥ ድምፅ በሚሰጥባቸው ውሳኔዎች ድምፅ የመስጠት መብት አላቸው፡፡
3. የኢትዮጵያን ፋርማሲዩቲካል ጆርናል፣ፋርማ-ፎረም እና ሌሎች የማኅበሩ ህትመቶችን በነጻ ወይንም በልዩ ሁኔታ ለአባላት ተብሎ በተወሰነ አነስተኛ ክፍያ ያገኛሉ፡፡
4. የማኅበሩ አባላት መሆናቸውን በጽሑፍ መግለጽ ይችላሉ፣ ማኅበሩም ግዴታቸውን ለተወጡ አባላት አባልነታቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ግዴታ አለበት፡፡
5. ማኅበሩ ለአባላቱ የሚሰጣቸውን ሌሎች ጥቅማጥቅሞች በሙሉ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

### 10.2 የመደበኛ ተቋማዊ አባላት መብት

1. ማንኛውም የማኅበሩ መደበኛ ተቋማዊ አባል በተቋሙ ዋና ኃላፊ ወይም አንድ ሌላ ተወካይ አማካኝነት ማኅበሩ በሚያካሂዳቸው ሣይንሳዊ ኮንፈረንሶችና ሴሚናሮች መሣተፍ ይችላል፡፡
2. ከመደበኛ (ቋሚ) ኮሚቴዎች ውጭ ማኅበሩ በሚያቋቁማቸው ሌሎች ኮሚቴዎች ውስጥ በተወካያቸው አማካኝነት የመሣተፍ መብት አላቸው፡፡
3. ማኅበሩ የሚሠጣቸውን እንደ የሕትመት፣ቤተመጻሕፍት፣ክበብ የመሳሰሉ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች የመጠቀም መብት አላቸው፡፡ አገልግሎቱ የሚሰጠው የተቋሙ ሥራ አስኪያጅ ወይንም መስሪያቤቱ ለሚወክለው አንድ የተቋሙ ሠራተኛ ይሆናል፡፡

4. ለመደበኛ ተቋማዊ አባላት የሚደረጉ ማትጊያዎች ማኅበሩ በሚያወጣው መመርያ ይወሰናል፡፡
5. ድምጽ የመስጠት መብት የላቸውም፡፡

## 10.3 የልዩ ተቋማዊ አባላት መብት

1. ልዩ ተቋማዊ አባላት በንዑስ አንቀጽ 9.2 ላይ የተዘረዘሩት የመደበኛ ተቋማዊ አባላት መብት በሙሉ ይኖራቸዋል፡፡
2. ለልዩ ተቋማዊ አባላት የሚደረግ ተጨማሪ ማትጊያ ማኅበሩ በሚያወጣው መመርያ ይወሰናል፡፡
3. ድምጽ የመስጠት መብት የላቸውም፡፡

## 10.4. የተባባሪ አባላት መብት

1. ማኅበሩ በሚያካሂዳቸው ሳይንሳዊ ኮንፈረንሶችና ሴሚናሮች የመሳተፍ መብት አላቸው፡፡
2. ከላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ተባባሪ አባላት በማኅበሩ ማዕከላዊ ሥራ አስፈጻሚ እና ልዩልዩ ኮሚቴዎች ውስጥ የሚያገለግሉ አባላትን የመምረጥ እና ራሳቸውም የመመረጥ መብት የላቸውም፡፡
3. በማኅበሩ አሠራር ውስጥ ድምፅ በሚሰጥባቸው ውሳኔዎች ድምፅ የመስጠት መብት የላቸውም፡፡

## 10.5. የተማሪ አባላት መብት

1. ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሚሰሩ ስራዎች የመሳተፍና ለቅርንጫፍ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን የመጠቆም መብት አላቸው፡፡
2. ማኅበሩ በሚያዘጋጃቸው ስልጠናዎች፣ወርክሾፖችና ሌሎች ዝግጅቶች የመሳተፍ መብት ይኖራቸዋል፡፡
3. በማኅበሩ ውስጥ በየትኛው ደረጃ ለኮሚቴ አባልነት መምረጥም ሆነ መመረጥ አይችሉም፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9.5 ተ.ቁ.3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የመደበኛ አባላት የሚያገኙትን ሌሎች ጥቅማጥቅሞች ያገኛሉ፡፡

## 10.6. የክብር አባላት መብት

1. ማኅበሩ በሚያዘጋጀው ዓመታዊ ሳይንሳዊ ጉባኤ ልዩ ቦታ ተዘጋጅቶላቸው ጉባዔውን እንዲከታተሉ ይደረጋል፡፡
2. የክብር አባልነታቸውን የሚገልፅ የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል፡፡
3. ከመምረጥና መመረጥ፣እንዲሁም በማኅበሩ አሠራር ውስጥ ድምፅ በሚሰጥባቸው ውሳኔዎች ድምፅ ከመስጠት በስተቀር መደበኛ አባላት የሚያገኟቸውን ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ያገኛሉ፡፡ የመደበኛ አባልነት መስፈርትን የሚያሟሉ ከሆነ ግን የመምረጥ፣ የመመረጥና ድምጽ የመስጠት መብት ይኖራቸዋል፡፡

## 10.7. የልዩ አባላት መብት

1. የመደበኛ አባልነትን መሥፈርት የሚያሟሉ ልዩ አባላት ብቻ በማኅበሩ ማዕከላዊ ሥራ አስፈጻሚ  እና ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ውስጥ የሚያገለግሉ አባላትን የመምረጥ እና/ወይንም ራሳቸውም የመመረጥ መብት አላቸው፡፡
2. ልዩ አባልነታቸውን የሚገልፅ የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል፡፡
3. ከላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የመደበኛ አባልነትን መሥፈርት የማያሟሉ ልዩ አባላት መደበኛ አባላት የሚያገኟቸውን ጥቅማጥቅሞች ያገኛሉ፡፡

## 10.8. የእድሜ ልክ አባላት መብት

1. የዕድሜ ልክ አባልነታቸውን የሚገልጽ የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል፡፡
2. የመደበኛ አባላት የሚያገኟቸውን ጥቅማጥቅሞች በሙሉ ያገኛሉ፡፡

## <u>አንቀጽ11፡ የአባልነት ግዴታ</u>

**ማንኛውም የማኅበሩ አባል የሚከተሉትን ግዴታዎች መፈጸም ይጠበቅበታል፡፡**

1. በማኅበሩ ማዕከላዊ ሥራ አስፈጻሚ ወይንም በማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ የሚተላለፉ ውሳኔዎችን ማክበር፣
2. የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ ማክበርና ማስከበር፤
3. በማኅበሩ ውስጥ በኮሚቴ አባልነትም ሆነ በራስ ተነሳሽነት ማኅበሩን ማገልገል፣
4. የአባልነት ክፍያዎችን ወቅቱን ጠብቆ መክፈል፣

5. አድራሻን፣ወቅታዊ የሙያ ደረጃንና የሥራ አድራሻን ለማኀበሩ ማሳወቅ፣
6. በተሰማሩበት ዘርፍ የሙያውን ስነምግባር ማክበርና ማስከበር፤

## አንቀጽ12፡ የአባልነት መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች

1. ማንኛውም አባል የአባልነት ክፍያዎችን ወይንም መዋጮዎችን በወቅቱ መክፈል አለበት፡፡
2. የየዓመቱ ወርሃዊ የአባልነት ክፍያ እስከ ዓመቱ መጨረሻ (የማኀበሩ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ እስከሚካሄድበት ቀን) ድረስ ተከፍሎ መጠናቀቅ አለበት፡፡
3. ወቅቱን ጠብቆ ዓመታዊ ክፍያውን ያልከፈለ አባል የክፍያውን 10% ተጨማሪ አድርጎ በቅጣት መልክ መክፈል ይኖርበታል፣
4. ተቋማዊ አባላት ለመረጡት የአባልነት ደረጃ በሚከተለው ሠንጠረዥ መሠረት ይከፍላሉ፡፡

| | አካዳሚክ ተቋማት/ፋብሪካዎች | | አስመጪና አከፋፋይ | | ችርቻሮ ድርጅቶች | | የጤና ተቋማት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ልዩ | መደበኛ | ልዩ | መደበኛ | ልዩ | መደበኛ | ልዩ | መደበኛ |
| የምዝገባ ክፍያ | 250.00 | 250.00 | 250.00 | 250.00 | 150.00 | 150.00 | 150.00 | 150.00 |
| ዓመታዊ ክፍያ | 5000.00 | 3000.00 | 5000.00 | 3000.00 | 1000.00 | 500.00 | 1000.00 | 500.00 |

5. በአዲስ አባልነት ለሚመዘገቡ መደበኛ አባላት የመታወቂያ ብር 25.00 (ሃያ አምስት)፣የመመዝገቢያ ብር 100.00 (አንድ መቶ) እንዲሁም ወርሃዊ መዋጮ ብር 25.00 (ሃያ አምስት) ይከፍላሉ፡፡ በውጭ ሃገር የሚኖሩ መደበኛ አባላት ከተመዘገቡበት ቀን ጀምሮ መላኪያውን ሳይጨምር በየዓመቱ 100.00 (መቶ) የአሜሪካን ዶላር መክፈል አለባቸው፡፡ የመመዝገብያ ክፍያ 5 (አምስት) የአሜሪካን ዶላር መክፈል አለባቸው፡፡
6. ማንኛውም ተባባሪ አባል የመታወቂያ ብር 2 5 .00 (ሃያ አምስት)፣የመመዝገቢያ ብር 100.00 (አንድ መቶ) እንዲሁም ወርሃዊ መዋጮ ብር 20.00 (ሃያ) ይከፍላሉ፡፡ በውጭ ሃገር የሚኖሩ ተባባሪ አባላት ከተመዘገቡበት ቀን ጀምሮ መላኪያውን ሳይጨምር በየዓመቱ 50.00 (ሃምሳ) የአሜሪካን ዶላር መክፈል አለባቸው፡፡ የመመዝገቢያ ክፍያ 5 (አምስት) የአሜሪካን ዶላር መክፈል አለባቸው፡፡
7. የአባልነት መመዝገቢያ ክፍያ የአባልነት ቅፅ ተሞልቶ በሚቀርብበት ጊዜ ተከፋይ ይሆናል፡፡
8. ወርሃዊው የአባልነት መዋጮ (ክፍያ) በየወሩ ሊከፈል ይችላል፡፡ በየወሩ ለመክፈል አመቺ ካልሆነ ዓመታዊው የማኀበሩ ጠቅላላ ጉባዔ እስከሚካሄድበት ቀን ድረስ በአንድ ጊዜ

ወይንም በተለያየ ጊዜ መክፈል ይቻላል፡፡

9. የተማሪ አባላት የመመዝገቢያ አይከፍሉም፤የአባልነት መዋጮ በዓመት ብር 60.00 (ስልሳ ብር) ይከፍላሉ፡፡ አከፋፈሉም በዓመት ሁለት ጊዜ በየስድስት ወራቱ ብር 30.00 (ሰላሳ ብር) መክፈል አለበት፡፡
10. ልዩ አባላት ብር 25,000.00 (ሃያ አምስት ሺህ) በአንድ ጊዜ ክፍያ መክፈል ይጠበቅባቸዋል፡፡
11. የመመዝገቢያ ክፍያው ከሚፈፀምበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ የተከታታይ አስር ዓመታት የአባልነት ክፍያ በአንድ ጊዜ የሚከፍል መደበኛ አባል የእድሜ ልክ አባል ሆኖ ይመዘገባል፡፡
12. የክብር አባላት የመመዝገቢያም ሆነ ዓመታዊ መዋጮ የመክፈል ግዴታ የለባቸውም፡፡
13. የመተዳደሪያ ደንቡ በማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲሻሻል ሲደረግ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የአባልነት መዋጮዎችና ክፍያዎች መጠን በማዕከላዊ ሥራ አስፈጻሚ አቅራቢነት በጠቅላላ ጉባዔው እንዲወሰን ይደረጋል፡፡
14. የመተዳደሪያ ደንቡ በሌሎች ጉዳዮች ምክንያት እንዲሻሻል ለጠቅላላ ጉባዔው የማይቀርብ ከሆነ የአባልነት መዋጮዎችና ክፍያዎች መጠን በማዕከላዊ ሥራ አስፈጻሚ አቅራቢነት በጠቅላላ ጉባኤው ሊወሰን ይችላል፡፡

## አንቀጽ13፡ የአባልነት ጥያቄ አቀራረብና ምዝገባ

1. ማንኛውም የማኅበሩ አባል ለመሆን የሚፈልግ ሰው ወይንም ድርጅት ለዚሁ አገልግሎት በተዘጋጀው ቅጽ መሠረት ማመልከቻውን በአቅራቢያው ለሚገኝ የማኅበሩ ቅርንጫፍ ወይንም ለማኅበሩ ዋና ጽ/ቤት ያቀርባል፣
2. ማመልከቻው የቀረበው ለማኅበሩ ቅርንጫፍ ከሆነ የቅርንጫፉ ስራ አስፈጻሚ የጥያቄውን አግባብነት ከመረመረ በኋላ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው አመልካቹን በጊዜያዊ አባልነት መዝግቦ ለማዕካላዊ ጽ/ቤት ይልከዋል፡፡
3. የማዕከላዊ ሥራ አስፈጻሚ በዓመቱ ውስጥ የቀረቡለትን የአባልነት ጥያቄዎች መርምሮ ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ያስፀድቃል፡፡
4. የክብር አባል እጩ በማዕከላዊ ሥራ አስፈጻሚ አቅራቢነት በጠቅላላ ጉባዔው ተቀባይነት ሲያገኝ የክብር አባል ሆኖ ይመዘገባል፡፡
5. ለመደበኛ አባል፣ተባባሪ አባል እና የተማሪ አባል የመታወቂያ ካርድ ከማኅበሩ

ይሰጣቸዋል፡፡ ለልዩ አባል፣የእድሜ ልክ አባል እና የክብር አባል ከመታወቂያ ካርድ በተጨማሪ የአባልነት የምስክር ወረቀት ከማኅበሩ ይሰጣቸዋል፡፡ ለተቋማዊ አባላት ደግሞ የአባልነት የምስክር ወረቀት ከማኅበሩ ይሰጣቸዋል፡፡

## አንቀጽ14፡ አባልነት የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች

### 14.1. ከአባልነት ስለመታገድ

1. የማዕከላዊ ሥራ አስፈጻሚው አንድን አባል በቂ በሆነ ምክንያት ማገድ ይችላል፡፡ ስለ ሁኔታውም ለጠቅላላ ጉባዔ አቅርቦ እገዳው እንዲቀጥል ወይም እንዲነሳ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
2. አንድ አባል በማዕከላዊ ሥራ አስፈጻሚ ከአባልነት ሲታገድ የታገደበት ምክንያት ተገልጾ ይጻፍለታል፡፡ ለዚህም መልስ የመስጠት መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ከማዕከላዊ ሥራ አስፈጻሚው የሚደርሰው እገዳ ጊዜያዊ ሲሆን ውሳኔው ቋሚ የሚሆነው በጠቅላላ ጉባዔ ሲፀድቅ ብቻ ነው፡፡
3. ለተከታታይ ሁለት ዓመታት የአባልነት ክፍያ ያልከፈለ አባል በሶስተኛው አመት መጀመሪያ ወር ላይ ማስጠንቀቂያ ይጻፍለታል፡፡
4. በማኅበሩ ውሳኔ የታገደ አባል ሁኔታው የተሻሻለ መሆኑ ጠቅላላ ጉባዔው ካመነበት እገዳውን በማንሳት እንደገና በአባልነት ሊቀበለው ይችላል፡፡
5. አንድ አባል ቢበዛ ለአንድ ዓመት ከታገደ በኋላ የእገዳው ምክንያት ተመርምሮ እንደገና በአባልነት እንዲቀጥል ወይም ከአባልነት ሙሉ በሙሉ እንዲሰናበት ይደረጋል እንጅ ከአንድ ዓመት በላይ በእገዳ ሊቆይ አይገባም፡፡ የተደረገው ጊዜያዊ እገዳ በሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ ካልተሰጠው እገዳው እንደተነሳ ይቆጠራል፡፡

### 14.2 ከአባልነት ስለመሠናበት

1. ማንኛውም አባል ከሁለት ዓመት በላይ የአባልነት ክፍያውን ያለ በቂ ምክንያት በማቋረጡ ከታገደ በኋላ ማሳሰቢያዎች ደርሰውት ለመክፈል ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር ከአባልነት ይሠናበታል፡፡
2. ማንኛውም አባል የሙያ ሥነ-ምግባርን የሚያጎድፍ ተግባሮችን የፈጸመ ወይም ሙያውን በተመለከተ ወንጀል ፈጽሞ በፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠው እንደሆነ ከአባልነት ይሠናበታል፡፡ የፍርድ ቤት እገዳው ከተጠናቀቀ በኋላ ግን እንደ አዲስ አባል መመዝገብ

ይችላል፡፡

3. ከማኅበሩ የተሠናበተ አባል ቀደም ብሎ የከፈለው ገንዘብ ተመላሽ አይሆንለትም፡፡ ከዓመታዊ የአባልነት ክፍያ ውጭ ከማኅበሩ የሚፈለግበት እዳ ካለም የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡

14.3 አባላት ራሳቸውን ከአባልነት ስለሚያገሉበት

1. ማንኛውም አባል በራሱ ፈቃድና ውሳኔ ከማኅበሩ አባልነት ራሱን ሊያገል ይችላል፣ይህንንም ለማዕከላዊ ሥራ አስፈጻሚ በቅድሚያ በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
2. ማንኛውም አባል ከሶስት ዓመት በላይ የአባልነት ክፍያውን ያለበቂ ምክንያት ሲያቋርጥ ራሱን ከአባልነት እንዳገለለ ይቆጠራል፡፡
3. ማኅበሩን በፈቃዱ የለቀቀ ማንኛውም አባል ቀደም ብሎ የከፈለው መዋጮ አይመለስለትም፡፡ ከማኅበሩ የሚፈለግበት እዳ ካለም ማጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡
4. በፍቃዱ የወጣ አባል እንደገና አባል ለመሆን ጥያቄ አቅርቦ ከተፈቀደለት እንደ አዲስ (ጀማሪ) አባል ይመዘገባል፡፡ አሳማኝና በቂ ምክንያት ካልቀረበ በስተቀር በዚህ ዓይነት ሁኔታ እንደገና መመዘገብ የሚቻለው ለአንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡